የሰ/መ/ቁ. 36777

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ወንድምአገኝ ዘውዱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ 1/ አቶ ታፈሠ ወንድአፍራሽ

2/ ወ/ሮ በለጤ አምደመስቀ ል ሁሉም } ቀርበዋል

3/ ወ/ሮ ቆንጅት ምንዳሁን

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የኑዛዜ አፃፃፍ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሟች ውብዬ ምንዳሁን የተውት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ለፍ/ቤቱ አመልክተው ኑዛዜው ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ በኂላ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሃሰተኛ ነው፤ ተናዛዥዋ ራሣቸውን በሣቱበት ጊዜ የተደረገ ነው፤ ሟች መፃፍ የሚችሉ ሆነው ሣለ በአሻራቸው መፈረማቸው ኑዛዜውን እንዳላደረጉ ያሣያል፤ በኑዛዜው በግልጽ አልተነቀልንም በማለት ኑዛዜው ውድቅ እንዲደረግ አቤቱታቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት አቅርበዋል፡፡ አመልካችም ቀርበው ኑዛዜው ውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ነው፤ ሟች በአሻራ ቢፈርሙም በውል አዋዋይ እና በምስክሮቹ ፊት ስለተደረገ ተገቢ ነው፤ ተጠሪዎች ተወላጆች ስላልሆኑ ከውርስ የተነቀሉበት ምክንያት ሊገለፅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ኑዛዜው በታይፕ ተጽፎ በምስክሮች ፊት ተነቦ ምስክሮችም ወዲያው መፈረማቸውን፣ ምስክሮቹ ችሎታ ያላቸውና አማርኛ ቋንቋም እንደሚችሉ፣ ሟችም ፊርማቸውን እንዳኖሩበት ተረጋግጧል፤ የምስክሮቹም ብዛት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት በቂ ነው፤ የሟች የአእምሮ ሁኔታ ደህንነትን በተመለከተ ኑዛዜውን ያስፈፀሙት ኃላፊ በምስክርነት ተጠርተው አረጋግጠዋል፤ ስለዚህ ኑዛዜው የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ የቀድሞው ውሣኔ አይሻርም በማለት የተጠሪዎችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህንን ውሣኔ በመቃወም ተጠሪዎች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ በ2 ምስክሮች መፈረሙ በቂ የሚሆነው ከምስክሮቹ አንዱ ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው አካል ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በኑዛዜው ላይ ከፈረሙት ሁለት ምስክሮች ውስጥ አንዳቸውም የውልና ምዝገባ ጽ/ቤት ሠራተኛ ስላልሆኑ ኑዛዜው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 የተቀመጠውን መስፈርት አያሟላም ስለሆነም አመልካች የሟች ውብዬ ምንዳሁን የኑዛዜ ወራሽነት መብት የላቸውም ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

አመልካችም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም ኑዛዜው የተደረገው ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት በአ/አበባ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመሆኑ በበቂ ምስክር ተረጋግጧል፤ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉትም በነፃ ፍላጎታቸው ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው ኑዛዜው በሕግ የተመለከተውን ስርዓት አልተከተለም፤ ሟች ኑዛዜውን የሰጡት ጤነኛ በነበሩበት ሰዓት አልነበረም ሟች የተማሩ ስለነበሩ በጣት መፈረማቸው በጠና መታመማቸውን ያሣያል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትና ይህም ችሎት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲጣራ ያደረገበት ነጥብ ሟች ውብዬ ያደረጉት ኑዛዜ በሕጉ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላል አያሟላም የሚለው ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባው ስርዓቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በ4 ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ፣ ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ፣ ሁለት ምስክሮች የፈረሙበት፣ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ኑዛዜውን አረጋግጦ የፈረመበት፣ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚገልጽ እና ተናዛዥዋ የጣት አሻራቸውን ምስክሮቹ ደግሞ ፊርማቸውን ያኖሩበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ሥር የተመለከቱትን ስርዓቶች ያሟላ ነው፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው የህጉን ሥርዓት አልተከተለም ያለው በኑዛዜው ላይ የተመለከቱት ሁለት ምስክሮች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ሠዎች አይደሉም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ምስክሮች ተብለው የተፃፉት ሁለት ሠዎች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው የተደረገው ከሁለቱ ምስክሮች በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ፊት፣ ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ነው፡፡ ምንም እንኳን እኚህ ሰው ምስክር ተብለው ባይገለፁም ሟች ኑዛዜውን በነፃ ፈቃዳቸው ሲሰጡና ኑዛዜውም ሲነበብ አይተው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል፡፡ የምስክሮች ዋና አስፈላጊነትም ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜ ቃሉም የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው አረጋግጠው ፊርማቸውን ያኖሩ በመሆኑ ምስክር ተብለው ስማቸው ባለመገለፁ ብቻ ምስክር አልነበሩም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ከምስክሮቹ አንዱ ደግሞ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ከሆነና ኑዛዜው ይኸው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ከሆነ ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ መሆናቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ በመሆኑ አመልካች የሟች ውብዬ ምንዳሁን የኑዛዜ ወራሽ አይደሉም በማለት የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ነው፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47307 በ01/09/99 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31022 በ28/06/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡

2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08063 በ4/08/98 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፤ ሟች አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ በመሆኑ አመልካች የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ